UNHCR
United Nations High Commissioner for Refugees
Haut Commissariat des Nations Unies pour les réfugiés

# የደብሊን ደንብን የሚመለከት መረጃ ዓለም አቀፍ ከለላ ለሚጠይቁ አመልካቾች የተዘጋጀ

## የደብሊን ደንብ ምንድን ነው?

አውሮፓ ውስጥ የሚገኙ ሐገራት የጥገኝነት ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የሚስችሉ የጋራ ደንቦችን አዘጋጅተዋል። የዚህ ስርዓት አንዱ አካል ደግሞ የደብሊን ደንብ ነው። የደብሊን ደንብ አውሮፓ ውስጥ ከሚገኙት 32 ሃገራት ወይም "የደብሊን ሃገራት" መካከል የእርስዎን የጥገኝነት ማመልከቻ በተለያዩ መስፈርቶች (ከታች ይመልከቱ) መዝኖ ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት ያለበት ሃገር የትኛው እንደሆነ የሚደነግግ ነው።

### "የደብሊን ሃገራት"

ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ክሮሽያ፣ ቆጵሮስ፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ዴንማርክ፣ ኢስቶኒያ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ግሪክ፣ ሐንጋሪ፣ አይስላንድ፣ አየርላንድ፣ ጣሊያን፣ ላትቪያ፣ ሊችተንስታይን፣ ሊትዌኒያ፣ ሉክዘምበርግ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድ፣ ኖርዌይ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ ሮማኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ስሎቬኒያ፣ ስፔን፣ ሰዊድን፣ ስዊዘርላንድ እና ዩናይትድ ኪንግደም ናቸው።

ይህ ማለት በአንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች ውስጥ እርስዎ ባሉበት ሃገር እንዲቆዩ ሊፈቀድልዎት ይችላል፤ ለምሳሌ እዚህ ቤተሰብ ካለዎት፣ ወይም ወደ ሌላ ሃገር አስተማማኝ፣ ነጻና መደበኛ በሆነ መንገድ ከተዛወሩ፣ ለምሳሌ እዚያ ቤተሰብ ካለዎ ማለት ነው።

እርስዎ ወደ ሌላ ሃገር የሚዛወሩባቸው ምክንያቶች ካሉና ይህም ጥያቄ በዚያ ሃገር ተቀባይነት ካገኘ፣ የጥገኝነት ማመልከቻዎ የሚመረመረው በዚያው ሃገር ይሆናል። ዕድሜዎ በአዋቂ የእድሜ ክልል ውስጥ ከሆነ፣ በደብሊን ደንብ መሰረት የቤተሰብ ውህደት የሚፈቀደው በሌላ ሃገር ውስጥ የሚገኘው የቤተሰብ አባል እርስዎን ለመቀበል ፈቃደኛ መሆኑን በጽሁፍ ማረጋገጫ ሲሰጥ ብቻ ነው።

## ወደ ሌላ የደብሊን ሃገር በሕጋዊ መንገድ ለመሄድ የሚችሉት በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡

- ልጅ ከሆኑ (ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ)። ከእናትዎ ወይም ከአባትዎ ወይም የእርስዎ ኃላፊ የሆነ ሌላ አዋቂ ሰው ጋር ካልሆኑ። የሚከተሉት ካለዎት ወይም አለ ብለው ካሰቡ
  - በሌላ የደብሊን ሃገር ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚኖር አባት፣ እናት፣ የእርስዎ ኃላፊ የሆነ ሌላ አዋቂ ሰው፣ ወንድም፣ እህት፤ ወይም፤
  - በሌላ የደብሊን ሃገር ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚኖርና እርስዎን መንከባከብ የሚችል አክስት፣ አጎት ወይም አያት

  እንዲሁም
  - ወደዚያው ሃገር ሄደው እነርሱን ለመቀላቀል የሚፈልጉ ከሆነ ነው።

- ዕድሜዎ በአዋቂ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሆነው በሌላ "የደብሊን ሃገር" ውስጥ የሚኖር የትዳር ጓደኛ፣ አጋር፣ ልጅ (ከ18 ዓመት በታች ዕድሜ ያለው) ካለዎ። እርሱን/እርሷን ለመቀላቀል የሚፈልጉ ከሆነ። በዚያ ሃገር ውስጥ የጥገኝነት ጥያቄ ካቀረበ/ካቀረበች ወይም ለጥገኝነት ማመልከቻው/ዋ አዎንታዊ ምላሽ ከተሰጠው/ጣት።

- "ከደብሊን ሃገር" የተሰጠ ሕጋዊ የመኖሪያ ሰነድ/ቪዛ ወይም ከሁለት ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱ ያበቃ የመኖሪያ ሰነድ ወይም ከስድስት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱ ያበቃ ቪዛ ካለዎትና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ "ከደብሊን ሃገራት" ግዛት ለቅቀው ካልወጡ።

- ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ አዲስ የተወለደ ልጅ ካለዎ፣ ከባድ የአካል ጉዳት ካለብዎ፣ የከፋ ሕመም ካለብዎ ወይም አረጋዊ ከሆኑ እና በሌላ "የደብሊን ሃገር" ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚኖር ወላጅ፣ እህት ወይም ወንድም ወይም ልጅ ካለዎት። እርሱን/እርሷን ለመቀላቀል የሚፈልጉ ከሆነ። ይህ ግለሰብም እርስዎን ለመርዳት የሚችል ከሆነ።

- ነፍሰ ጡር የሆነች፣ አዲስ የተወለደ ልጅ ያላት/ያለው፣ ከባድ የአካል ጉዳት ያለበት፣ በጠና የታመመ ወይም ዕድሜው የገፋና በሌላ "የደብሊን ሃገር" ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የሚኖር አዋቂ ልጅ፣ ወንድም ወይም እህት ወይም ወላጅ ካለዎት። ይህን ግለሰብ ለመቀላቀል የሚፈልጉ ከሆነ። ይህን ግለሰብ ለመርዳት የሚችሉ ከሆነ።

- በሰብዓዊ ጉዳዮች ምክንያት በተለይም ደግሞ በባሕላዊና የቤተሰባዊ ጉዳዮች ምክንያት በሌላ "የደብሊን ሃገር" ውስጥ የሚገኝ የቤተሰብ አባልዎን ለመቀላቀል የሚፈልጉ ከሆነ። ሌላኛው ሃገርም እርስዎን ለመቀበል ከተስማማ።

## ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ካጋጠመዎ የሚከተሉትን መፈጸም ያስፈልግዎታል

- በአሁኑ ጊዜ በሚገኙበት ሃገር ባለስልጣናት ዘንድ ቀርበው የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ።
- ለባለስልጣናቱ ያቀረቡትን ጥያቄ ደረጃ ዘንድ፡ ያሉበትን ሁኔታ አስረድተው እርስዎንም ሆነ የቤተሰብ አባላትዎን የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎች/ሰነዶች በሙሉ (ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ የቤተሰብ ትስስር ማስረጃ፣ የመኖሪያ ፈቃድ፣ ወዘተ...) በተቻለ ፍጥነት ማቅረብ/ማሳወቅ።

## የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብተው ከሆነ፤ በሌላ "የደብሊን ሃገር" በኩል አልፈው ወይም ኖረው ከሆነ

ወደዚያ ሃገር ሊመለሱ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች፡

- በአሁኑ ጊዜ ወደሚኖሩበት ሃገር ከመግባትዎ በፊት በሌላ "የደብሊን ሃገር" ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻ አቅርበው ከሆነ፤ ወይም
- እርስዎ ወደ አውሮፓ የገቡት ከሌላ "የደብሊን ሃገር" መጥተው መሆኑን ወይም በሌላ "የደብሊን ሃገር" ውስጥ ቢያንስ ለ5 ወራት ያህል መኖርዎትን የሚያሳይ ማስረጃ (ለምሳሌ የጣት አሻራዎ) ከተገኘ፤

እና

- ወደ ሌላ "የደብሊን ሃገር" ዝውውር ለመጠየቅ የሚያበቃ በቂ ምክንያት ከሌለዎ (ከላይ ያሉትን መስፈርቶች ይመልከቱ)።

### የደብሊን አሰራር ደንብ

- ዕድሜዎ ልጅ ከሆነ (ከ18 ዓመት በታች ከሆኑ)፣ ባለስልጣናቱ የሚያግዝዎት ሰው ያፈላልጋሉ (ወኪል/ሞግዚት/ጠበቃ)።
- የጣት አሻራዎን እንዲሰጡ ይጠየቃሉ (ዕድሜዎ ከ14 ዓመት በላይ ከሆነ)።
- የአስተርጓሚ ድጋፍ ማግኘት የሚችሉ ሲሆን አስተርጓሚ ሲያስፈልግዎ እንዲቀርብልዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- ለጥያቄዎ እገዛ የሚያደርጉልዎን የተመደ የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) ማናገር ይችላሉ (እባክዎ የግንኙነት መረጃውን በስተጀርባ ላይ ይመልከቱ)።
- በሚኖሩበት ሃገር ባለስልጣናት በኩል ቃለ መጠይቅ የሚደረግልዎት ሲሆን አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች እና/ወይም ሰነዶች እንዲያቀርቡም ይጠየቃሉ።
- ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች መካከል አንዱ ካጋጠመዎት፣ የሚዛወሩበት ምክንያት ካለዎት እርስዎ የሚኖሩበት ሃገር ባለስልጣናት ወደሌላኛው ሃገር ባለስልጣናት ጥያቄ ሊልኩ ይችላሉ፤ እንደዚሁም እርስዎ የሚቆዩበት ምክንያት ካለዎት ማመልከቻዎን ለመመርመር ሊወስኑ ይችላሉ።
- ጥያቄዎ የተላከበት ሃገር ውሳኔ ምን እንደሆነ ይነገርዎታል።
- ከማመልከቻ ጀምሮ እስከ ዝውውር ያለው ሂደት (ያኛው ሃገር ከተስማማ) የሚፈጀው ጊዜ ይለያያል። በተለመደው አሰራር ከ1 እስከ 11 ወራት የሚፈጅ ቢሆንም ከዚህ ጊዜ በላይ የፈጀባቸው ሁኔታዎችም ነበሩ።

#### በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩዎታል፡

- ባሉበት ሃገር ውስጥ የመቆየት።
- የማረፊያ ቦታ፣ ምግብ፣ መሰረታዊ የጤና እንክብካቤ፣ አጣዳፊ ሕክምና፣ ወዘተ.. የማግኘት
- ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ፣ ትምህርትዎን መቀጠል ይችላሉ።

# የግንኙነት መረጃዎች

**UNHCR Paris**
46/48 rue Lauriston
75116 Paris
FRANCE
Tél. + 33 (0)1 44 43 48 58
Fax : + 33 (0)1 44 43 48 61
Email : frapa@unhcr.org

**UNHCR Calais**
Tél. +33 (0)6 03 46 48 03

**UNHCR London**
10 Furnival Street,
EC4A 1AB London
UNITED KINGDOM
Tel. +44 203 761 9500
Email: gbrlo@unhcr.org

UNHCR
United Nations High Commissioner for Refugees
Haut Commissariat des Nations Unies pour les réfugiés